ምድብ አንድ (የሙዓለ ሕፃናት ተማሪዎች)

9 ኛ ሳምንት

# ይስሐቅም ያዕቆብን ባረከው

## ዓላማ

❖ የበረከትን ጥቅም ማመር

## ምንባብ

❖ ዘፍጥ.27

## መግቢያ

❖ ይስሐቅን ታስታውሱታላችሁ? እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለሳራ የሰጣቸው የቃል ኪዳን ልጅ ነበር፡፡

❖ በዛሬው ትምህርታችም ልጁን ያዕቆብን የባረከውን ልዩ በረከት እንማራለን፡፡

## ትምህርቱ

❖ የአብርሃም እና የሳራ የቃል ኪዳን ልጃቸው ይስሐቅ ርብቃ የተባለች ሚስትም አገባ፡፡ ይስሐቅ እና ርብቃ ዔሳው እና ያዕቆብም የተባሉ ሁለት ልጆች ነበሯቸው፡፡ መንትዮች ሲሆኑ ዔሳው መጀመሪያ ስለተወለደም ታላቅ ነበር፡፡

❖ የበኩር ልጅ በመሆን ከአባቱ የሚያገኘው ልዩ በረከትም ነበር፡፡

❖ ዔሳው አንድ ቀን በጣም ተርቦ ከአደን ወደ ቤቱ ተመለሰ ያዕቆብ ወጥ እየሠራም አገኘውና ከሚሠራው እንዲያበላው ጠየቀው፡፡ ያዕቆብም ብኩርናውን ሥጠኝና አበላሀለው አለው፡፡ ዔሳውም ብኩርናውን ሰጥቶ በላ፡፡

❖ ይስሐቅ ሲያረጅም ያዕቆብ ከአባቱ የብኩርናውን በረከት ወሰደ፡፡ ዔሳው ግን በረከቱን ስለተዋት አላገኛትም፡፡

❖ እግዚአብሔርም በይስሐቅ በረከት ያዕቆብን ባረከው፡፡

**ጥያቄ፣** 1. የይስሐቅ አባት ማነው? ሀ. ያዕቆብ ለ. አብርሃም ሐ. ዔሳው

2. የይስሐቅ እና የርብቃ የመጀመሪያ ልጅ ማን ነበር? ሀ. ያዕቆብ ለ. ዔሳው

3. የበኩር ልጅ የሚያገኘው ልዩ ነገር ምንድን ነበር? ሀ. መኪና ለ. ቤት ሐ. በረከት

4. የብኩርናን በረከት ከአባቱ ያገኘው ማንነው? ሀ. ያዕቆብ ለ. ዔሳው

**ተግባር:-** 1. ከጀርባ ያለውን ሥዕል አስተውሉ ሌላ የመስቀል ሥዕልም ሳሉ፡፡

2. የሚከተለውን መዝሙር ከመምህር ጋር ተለማመዱ፡፡

## መዝሙር

ለጌታዬ ለእግዘአብሔር ስላደረገልኝ ምን እከፍለዋለሁ?

ምሥጋና ነው እንጂ (2) ሌላ ምን እላለሁ (4)



ይቆየን፡፡